## ጉባኤ ኤፌሶን (431 ዓ.ም)

በጉባኤ ኤፌሶን የምናያቸው:-

ሀ/ ጉባኤው እንዲደረግ ምክንያት የሆነው የንስጥሮስ ክሕደት፤
ለ/ የቅዱስ ቄርሎስ የምስጢረ ሥጋዌ ትምህርትና በንስጥሮስ ክሕደት ላይ ያደረገው ዘመቻ፤
ሐ/ የኤፌሶን ጉባኤ መሰብሰብና ያስተላለፈው ውሳኔ ናቸው::

ከተቀረቆች ጀምሮ የሃይማኖት ጭቅጭቅ ከአደባባይዋ ተለይቷት የማያውቀው ቍስጥንጥንያ፣ አሁንም በሊቀ ጳጳስዋ በንስጥሮ የክሕደት ትምህርት ብዙ ችግር ደርሶባታል:: ንስጥሮስ «ኤፍፐሬፐዮስ» በሚባል የአንጾኪያ ገዳም የሚኖር ግሪካዊ መነኩሴ ነበር:: ዲቁናና ቅስና የተሾመውም በአንጾኪያ ነበር:: ድምፀ መልካምና ንግግር አሳማሪ እንደነበር ይነገርለታል፤ ከፍተኛ ትምህርቱን የተማረው በአንጾኪያ ትምህርት ቤት ከዲያድርስ (ዲዮዶሮስ) ነው:: ዲያድርስ በቂልቅያ በምትገኝ በጠርሴስ ሊቀ ጳጳስ ነበር (378-394):: ንስጥሮስ ብቻ ሳይሆን (የሞብሱኤስቲያው) ቴዎድሮስ፣ ዮሐንስ ዘአንጾኪያና (የቂሮስ) ቴዎዶሪጦስ (ቲዎዶሪቶስ) የተማሩ ክርሱ ነው::

ይኸው ዲያድርስ እምነቱም ትምህርቱም በምስጢረ ሥጋዌ ክርስቶስን ከሁለት ከፍሎ አንዱን ወልደ ዳዊት ሌላውን ወልደ እግዚአብሔር ነው ብሎ ያምን ነበር:: በሱ አባባል ከማርያም የተወለደው ወልደ ዳዊት ከእግዚአብሔር አብ የተወለደው ወልደ እግዚአብሔር ነው:: ከእግዚአብሔር አብ የተወለደው ቃል ከማርያም በተወለደው ወልደ ዳዊት አደረበት:: ስለዚህ የዳዊት ልጅ ለእግዚአብሔር ልጅ መቅደስ ማኅደር ነው:: ዕቃ በጨርቅ እንዲጠቀለል መጽሐፍ በማኅደር እንደሚያድር፤ እንዲህ እያለ በማስተማሩ መላዋን አንጾኪያን በምንታዌ ትምህርት አጥለቅልቋት ነበር:: አንጾኪያ በሉቅያኖስ የተነሣ በምሥጢረ ሥላሴ መዓረገ መለኮትን በማበላለጥ ለአርዮሳውያን መፍለቂያ እንደሆነች፣ አሁንም በዲያድርስ የተነሣ በምስጢረ ሥጋዌ የሁለት ባሕርይ ትምህርት ምንጭ እንደሆነች የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የሚከታተሉ ሁሉ ሊያስተውሉት ይገባል::

በሉቅያኖስ ትምህርት የተመረዘችው የአንጾኪያ ትምህርት ቤት የምትፈለፍላቸው ደቀ መዛሙርት ሁሉ፣ በምስጢረ ሥላሴው ስሕተታቸው ላይ የዲያድርስን የኀድረት ትምህርት ሲቀላቀሉበት «በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ» እንደሚባለው ቤተ ክርስቲያን በጣም ታወከች፤ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ቍ 14 «ወውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ» ያለውን ንባብ በእስክንድርያ ያሉ ሊቃውንት ለምስጢረ ተዋሕዶ አውራ ጥቅስ አድርገው ምስጢረ ሥጋዌን ከመዳን ምሥጢር ጋር አስማምተው ሲተረጕሙ የአንጾኪያዎቹ ደግሞ እንደ እስክንድርያ ትምህርት ቤት «ቃል ሥጋ ኮነ» ማለት ቃል ወደ ሥጋነት ተለወጠ ማለት ነው ውላጤን፣ ሚጠትን ያስከትላል ይሉ ነበር:: ለዚህም ምሳሌ የሚጠቅሱት በዘፍጥረት 19÷26፣ ዘጸ 4÷3 የሎጥን ሚስት ወደ ደንጊያነት መለወጥና የሙሴን በትር ወደ እባብነት መለወጥ የሚያመለክት ግስ ነው ይል ነበር:: ስለዚህ ኮነ የሚለው ግስ በነሱ አስተሳሰብ «ነሥአ» ተብሎ መተርጎም የሚያስፈልገው መሆኑን አጥብቀው ይከራከሩበት ነበር::

ጳውሎስ በገላትያ 4÷4 «እግዚአብሔር ልጁን ሰደደ ከሴትም ተወለደ» ያለው በእነሱ አተረጓጎም ይህ የተነገረው ቀጥታ ለሰው ነው:: ከሴት ለተወለደው ከሕግ በታች ኹኖ ለኖረው ነው ዕሩቅ ብእሲ ወልደ ዳዊት ላሉት ጳውሎስ ወልደ እግዚአብሔር ብሎ የሠየመውም ቃል ራሱን ዝቅ አድርጎ ስላደረበት ከሰው ኹሉ ተለይቶ የማደጎ ልጅነት፣ የጸጋ ልጅነት (ትርሲተ ወልድ) ተካፋይ መኾኑን ሲገልጥ ነው:: ዳግመኛም ጳውሎስ በፊልጵስዩስ መልእክቱ 2÷5-7 «ነሥአ አርአያ ገብር» ያለውን «ቃል በሥጋ አደረ» ለማለት እንዲመቻቸው መሪ ጥቅስ አድርገው ይጠቀሙበት ነበር:: ዮሐንስ «ቃል ሥጋ ኮነ» ቃለውን ውላጤን ያስከትላል ስለሚሉ፣ ከጳውሎስና ከዮሐንስ አንዳንድ ቃል ለቅመው፣ ቃል፣ እንደ ጳውሎስ አነጋገር «ሰው መስሎ ታየ» እንደ ዮሐንስም ኀደረ ላዕሌነ ወውስቴትነ» በመካከላችን ኖረ ይላሉ:: በዲያድርስና በተማሪዎቹ አስተሳሰብ ሰው መኾን ማለት» ሰው መስሎ መታየት ነው:: ይኸውም ምትሐት እንጂ ተዋሕዶ አይደለም፤ ይህንንም ወደ ፊት በንስጥሮስ ትምህርት እንመለከተዋለን::

ንስጥሮስ በአንጾኪያ የተማረውን የኹለት ባሕርይ ትምህርት የገለጠው የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ከኾነ በኋላ ነው:: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስረዳው ከ425-427 ዓ.ም የቍስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው ሱስንዮስ ቀዳማዊ ሲሞት በ428፣ ዓ.ም ንስጥሮስ የቍስጥንጥንያ ኤጲስ ቆጶስ ተባለ:: ንስጥሮስ የኀድረት ትምህርትን ለማስፋፋት አመች መስሎ የታየውም ይህ የሥልጣን ጊዜው ነበር:: ከዕለታት አንድ ቀን አቡነ ቀሲሱ አናስታቴዎስ (አንስጣቴዎስ) በቤተ ክርስቲያን ሲያስተምር የኹለት ባሕርይን ትምህርትና እመቤታችንም ወላዲተ አምላክ አትባልም ብሎ ገልጦ ተናገረ:: በዚህ ጊዜ ምእመናኑ ደነገጡ:: በዚህ ምክንያት ወደ ሊቀ ጳጳሱ ወደ ንስጥሮስ ቀርበው፣ ተሰምቶ የማይታወቅ ትምህርት በቤተ ክርስቲያናችን ተነገረብን ብለው አቤት አሉ፣ እሱ ግን ለዚህ ነገር አውራው ስለ ኾነ፣ የሕዝቡን አቤቱታ እንደፌዝ በመቍጠር አልተቀበላቸውም:: እንዲያውም ትምህርቱን በይፋ ለመቀጠል «ከማርያም የተወለደው ዕሩቅ ብእሲ ነው፤ ቃል በጥምቀት በዮርዳኖስ እስኪያድርበት ድረስ ወልደ ማርያም የቃል ማደሪያ ለመኾን ተወለደ «ሶበ ተራከቦ ወልደ እግዚአብሔር ለወልደ ማርያም በዮርዳኖስ፣ ረሰዮ አምላክ በጸጋ» ወይም ውሃ በቦይ እንደሚያልፍ ቃል በማሕፀነ ማርያም አለፈ፤ ስለዚህ ማርያም ወላዲተ ሰብእ ናት እንጂ ወላዲተ አምላክ አትባልም፣ እያለ በየደረሰበት ያስተምር ጀመር:: ይህንንም አሳቡን በምሳሌ ለማስደገፍ አንድንድ ምሳሌዎችን አቀርቧል:: ለምሳሌ ይላል ንስጥሮስ አንድ ንጉሥ ራሱን ለመሰወርና ከወታደሮቹም አንዱን ለመምሰል ቢፈልግ ልብሰ መንግሥቱን ትቶ የወታደሮቹን ልብስ እንደሚለብስ ራሱን በዚህ ዓይነት ከሰወረ በኋላ እንደ ጓደኛ ኹኖ ሊያነጋግራቸው እንደሚችል፣ ቃልም በሥጋ አድሮ በሥጋ ተሠውሮ ታየ ይህ በፈቃዱ ከወታደሮቹ እንደ አንዱ ለመምሰል የፈቀደው ንጉሥ ምንም እንኳ ንጉሣቸው ቢሆን፡ እነሱን ከመሰለ ሥርዓታቸውንም ማሟላት እንዳቀበት፣ የቃልም ሰው ሆኖ ሕገ ኦሪትን መፈጸም ከዚህ የተለየ ትርጉም አይሰጠውም ብሏል:: በአንቀጸ ተዋሕዶም የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ አካላዊ ነው እያለ መላልሶ ይናገር ነበር፤ ይህም ከእነ ቅዱስ አትናቴዎስ ትምህርት የተለየ አስተሳሰብ ነው፤ በእነሱ ትምህርት የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ ባሕርያዊ ነውና::

አካላዊ ተዋሕዶ ማለት በንስጥሮስና በመሰሎቹ ዘንድ ሥጋ ለቃል ማኅደሩ፣ ተሸካሚው፣ ልብሱ፣ መቅደሱ ነው ማለት ነው:: በዚህ አባባል ሰጪም ተቀባይም ቃል ነው ማለት የራሱን ለሥጋ የሰጠ የሥጋን የወሰደ:: ስለዚህ ቃልና ሥጋ በንስጥሮስ አስተሳሰብ የውድ፣ የፈቃድ እንደ ወዳጅ እንደ ጓደኛ አብረው ይኖራሉ እንጂ፣ ባሕርያዊ ተዋሕዶ የላቸውም:: ስለ እመቤታችንም መልሶ መላልሶ ማርያም ወላዲተ አምላክ አይደለችም፣ ዕሩቅ ብእሲን እንጂ፣ አምላክን አልወለደችም እያለ ይናገር ነበር:: እግዚአብሔር ከሰው ይወለድ ዘንድ አይቻልም እግዚአብሔር ከማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ተወለደ ማለት ስሕተት ነው፤ እግዚአብሔር የናቱን ጡት ጠባ የኹለት የሦስት ወር ልጅ ኾነ ዘመን ተቆጠረለት ብሎ ማስተማር በንስጥሮስ ዘንድ ትልቅ ክሕደት ነበር:: በንስጥሮስ አባባል አንድ የሚገርም ነገር ቢኖር፣ ከዚህ በታች የተናገረው ነው፣ «ስለ ኅዳሪው ማለት ስለ ቃል ክብር፣ ለማኅደሩ ለሥጋ እሰግዳለሁ፤ ስለ ኅዳሪው ማኅደሩን አከብራለሁ፤ ማርያምንም ወላዲተ አምላክ ብል በወለደችው ዕሩቅ ብእሲ ወይም አርአያ ገብር፣ ቃል ስላደረበት ብቻ ነው» ይል ነበር:: ለዚህ ኹሉ አስተሳሰቡ ድጋፍ የሚኾነው መስሎት፣ ስለ ሥጋዊ የሚያመለክቱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እየተሻማ ወስዷቸዋል:: ታዲያ ጥቅሶቹ መልሰው የራሱን ስሕተት የሚያሳዩ ናቸው::

ይህን የንስጥሮስን ትምህርት በመጀመሪያ የተቃወመችው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ነበረች:: ያን ጊዜ የነበረው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስ (412-444) በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ተጋድሎ ያደረገ ስለ ኾነ፣ ስለ ሕይወት ታሪኩና ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርቱ በመጠኑ እንመለከታለን:: ቅዱስ ቄርሎስ ትውልዱም ነገዱም የግብጽ አፍሪቃዊ (ኮፕት) ነው:: የተወለደው በ375 ዓ.ም በእስክንድርያ ነው:: ከሱ በፊት የእስክንድርያ ፓትርያርክ ለነበረው ለቴዎፍሎስ የእህቱ ልጅ ነው:: ያደገውም የተማረውም በእስክንድርያ መንበረ ፓትርያርክ ነበር:: ከሃይማኖት ትምህርቱ ጋር የዮናውያንን ቋንቋና የፍልስፍና ትምህርት አጠናቆ ካወቀ በኋላ፣ ገዳም ገብቶ ሲረዳ ቆይቶ ልብሰ ምንኩስና ለበሰ:: የምንኩስና ሕይወቱን አጠናክሮ ከሰው ተለይቶ በበረሀ ለአምስት ዓመታት ያህል የተባሕትዎን ገድል ተጋድሏል:: ምንም እንኳ ቄርሎስ አሳቡ በተባህትዎ ለመኖር ቢኾንም፣ በሙያውና በትሩፋቱ ቤተ ክርስቲያንን በበለጠ እንደሚያገለግል በመረዳት ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ አስጠርቶ አምጥቶ የዲቁናና የቅስና ማዕረግ ሾመው:: ከዚህም በማያያዝ በመንበረ ፓትርያርኩ የአስተዳደር ክፍል ሹም ኾነ በ412 ዓ.ም ቴዎፍሎስ ሲያርፍ ካህናትና ምእመናን ባንድ ድምጽ መርጠውት የመንበረ ማርቆስ 24ኛ ፓትርያርክ ኾነ:: (412-444):: ቅዱስ ቄርሎስ የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን ለ32 ዓመታት የመራ መንፈሳዊ አባት ነው:: ይልቁንም የኦርቶዶክስን እምነት ከጥፋት ለማዳን በኤፌሶን ጉባኤ ባደረገው ተጋድሎ፣ ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባቶችንና ሲኖዶሶች «ማኅተመ አበው» «የኦርቶዶክስ እምነት ጠበቃ» «ብርሃነ ዓለም» እያሉ ሰይመውታል፤ አሞግሰውታል:: ቅዱስ ቄርሎስ ብዙ መጻሕፍትን ጽፏል:: ከጻፋቸውም መጻሕፍት ውስጥ ከመናፍቃን ጋር የተከራከረባቸው አንቀጾች ናቸው፤ በኛም በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ ስለ ምስጢረ ሥጋዌና ስለ ምሥጢረ ሥላሴ የሚናገሩ የቄርሎስ መጻሕፍት አሉ:: የቄርሎስ ዕረፍት ሐምሌ 3 ቀን 444 ዓ.ም ነው:: (ሌሎች ግን ሰኔ 27 ቀን ነው ይላሉ) ስለ ቅዱስ ቄርሎስ ትምህርት በመጠኑም ቢኾን ከዚህ በታች እንገልጣለን:-

የትምህርቱ መልክና ጠባይ የቅዱስ አትናቴዎስንና የቀጰዶቅያን ሊቃውንት፤ የጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙን፤ የባስልዮስ ዘቂሣርያንና የጎርጎርዮስ ዘኑሲስን ይመስላል:: ምሥጢሩም ምሥጢረ ሥጋዌን የሚሰብክ ነው:: በእስክንድርያ አባቶች ዘንድ፣ ምሥጢረ ሥጋዌ የምሥጢራት ሁሉ በላይ ነው:: እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣልና:: ቄርሎስም እንደ አትናቴዎስ የምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርቱን የሚጀምረው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረውን የደፈረሰ ግንኙነትና የእግዚአብሔርን መግቦት እያስታወሰ ነው:: እግዚአብሔር የደስታና የደግነት ምንጭ መኾኑን ቄርሎስ መላልሶ ይናገር ነበር:: ሰው ወዳጅ ስለኾነ፣ በንጹሓን ልብ ያድራል፤ በፍጡርና በፈጣሪ መካከል ኃጢአት የወለደው ልዩነት ቢኖርም ከፍጡራን በመግቦት ተለይቶ የማያውቅ አምላክ መኾኑን ቄርሎስ ይመሰክር ነበር:: ስለዚህ ይላል ቄርሎስ ለአምላክ ሰው መኾን ዋናው ምክንያት፣ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ፣ ነጻ ኹኖ የተፈጠረ አዳም በስሕተቱ ነጻነቱን ስለ አጣ የተሰጠው ክብርም ስለ ተወሰደበት ከመራራቅም የተነሣ ፈጣሪውን እየዘነጋው ስለሔደ ሰውን ወደ ቀደመ ቦታው ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለስ ነው:: በጥንተ ተፈጥሮ የፈጠረውን ሰው እንደገና ሰው ኹኖ ሥጋ ለብሶ በሐዲስ ተፈጥሮ ፈጠረው::

ቄርሎስ በምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርቱ ሚጠትንና ውላጤን አጥብቆ ይቃወም ስለ ነበር የአንጾኪያ ትምህርት ቤት በእስክንድርያ ትምህርት ቤት ላይ የነበራትን የውላጤ ሐሜት ደምስሶታል:: በመዋዕለ ሥጋዌ፣ ቃል ከቀዳማዊነቱ፣ ከባሕርይ ክብሩ ቁልቁል አልተለወጠም፤ በዚያው በሉዓላዊነቱ የጠና ነው እንጂ:: ሰውን ለማዳን ሰው ቢኾንም፣ አርአያ ገብርን ቢነሣም፣ በፈቃዱ ያደረገው አትኅቶ ርዕስ መኾኑን ኹሉ እንዲያውቀው ቄርሎስ ያስተምር ነበር:: ከባሕርይ አባቱ ከአብ በአካል የተካከለ በባሕርይ በህልውና አንድ የኾነ ነው፤ አምላክነት ያልነበረው ኹኖ እንደ ሽልማት የተሰጠው አይደለም ያልነበረውንስ ያልነበረበትንስ አርአያ ገብርን ተዋሐደ ማለት ሰው ኾነ፤ ሥጋ ለበሰ፤ ከተዋሕዶ በኋላ ኹለት ግብር የሚሉትንም እንደ አርእስት እዚህ ላይ ይነቅፋቸዋል::

ቃል በማይመረመር መግቦቱ፣ ሰው ኹኖ ሥጋ ለብሶ ከኃጢአት በቀር ሰው የሚሠራውን ሁሉ ሠራ:: ሰው ሆነ፤ ሥጋ ስለ ለበሰ የሠራውን ኹሉ ለይቶ ከፋፍሎ ግማሹን ለመለኮት ግማሹን ለትስብእት ሰጥቶ መናገር ጠቅላላውን የምሥጢረ ሥጋዌን ጠባይ ይሰውጠዋል:: ሰው ሆነ ካልን የሰብእናን ሕግ መፈጸሙንም ማወቅ አለብን፤ ቃል ከሥጋዌ በፊት፣ በሥጋዌ ጊዜ፣ ከሥጋዌም በኋላ የማይለወጥ ነው:: ሰው ሆነ፤ ሥጋ ለበሰ፤ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ኾነ፤ ፍጹም ሰው መኾኑንም የምናውቀው ሰብአዊውን ኹሉ የራሱ በማድረጉ ነው:: ተዋሕዶውም ባሕርያዊ ነው፤ በከዊን የተደረገውን ባሕርያዊ ተዋሕዶ ካልተቀበልን፣ ኹለት ልጆች ከማለት አዘቅት ውስጥ እንገባለን:: ቃል የሥጋን ገንዘብ፣ የሥጋን ሀብት የራሱ ካደረገው፣ እንደገና የሌላ ሊኾን አይችልም:: ቄርሎስ ይህን ትምህርቱን ሲሰሙ ቃልና ሥጋን ጎን ለጎን አድርገው ወይም ኅዳሪና ማኅደር አድርገው ምንታዌን የሚያስተምሩ ኹሉ ደንግጠዋል::

ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ የምትባልበትንም ምክንያት ሲያስረዳ፣ ቄርሎስ እንዲህ ይላል:: ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ የምንላት፣ ቃል ከዊነ ቃልነቱን ከሷ ያገኘው ነው፤ ወይም የወልድ አካል የተገኘው ከእሷ ነው፣ «ለፌ እማርያም ለወልድ ከዋኔሁ» ብለን አይደለም:: በመግቦት ምሥጢሩ ሰውን ለማዳን ከእሷ በሥጋ ስለ ተወለደ ነው እንጂ:: ይህንኑ ትምህርት በመደጋገም ሲያስረዳ ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ ናት ብሎ የማይቀበል፣ ማርያም የወለደችው ዕሩቅ ብእሲ ነው የሚል፣ ምሥጢረ ሥጋዌ ያልገባው ነው ይላል:: የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ምስክር የኾነው ይህ ቅዱስ ቄርሎስ፣ የመናፍቃንን ሐተታ ወደጎን ትቶ «እግዚአብሔር ተወልዶ አዳነን» በማለት ሐሳቡን ኹሉ ያጠቃልል ነበር:: ሌሎችም ሊቃውንት እነ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ ስለመኾኗ በሚገባ መስክረዋል፤ «ቅድስት ድንግል ማርያምን፣ ወላዲተ አምላክ ብሎ የማያምን ከአምላክ

የተለየ ነው።» ይህም ማለት እንደ ፎጢኖስ (ፎቲኖስ) የቃልን ቅድመ ዓለም ህልውና ክዶ፣ የወልድ (የቃል) መኖር የተጀመረው ከማርያም በተወለደ ጊዜ ነው ማለት አይደለም።

ቃል ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት ተወለደ፤ ድኅረ ዓለም ከድንግል ማርያም ያለ አባት ተወለደ እንጂ። ቄርሎስ ከሱ በፊት እንደ ነበሩ መምህራን እንደነ አትናቴዎስ፣ «ቃል ከሥጋዌ በፊትና ቃል በሥጋዌ ጊዜ» እንዴት እንደሆነ ለይቶ ጠንቅቆ ይናገራል፤ ምሥጢር አያፋልስም። ለምሳሌ የሥግው ቃል የማዳን ሥራውን ሲያስተምር «እግዚአብሔር ለሰው ብሎ መከራ መቀበሉን እግዚአብሐር ለሰው ብሎ መሞቱን ይናገራል። ይህን በሚልበት ጊዜ እግዚአብሔርን ገዳይ እንዳይሉት፣ በዓለመ ሥጋዌ፣ በመዋዕለ ሥጋዌ፣ በሥጋ ርስት ሥግው ቃል የተሸከመውን መከራ መስቀል መኾኑንም አብራርቶ ያስረዳል። (እብራ 2÷9፣ 1ኛ ጴጥ 4÷1) ሐመ ዘኢያሐምም፤ ሞተ ዘኢይመውት (የማይታመም ታመመ፤ የማይሞት ሞተ)፤ ማለትም የሥጋን ሐማሚ፣ መዋቲ ባሕርይ በተዋሕዶ የራሱ አድርጎ እግዚአብሔር ቃል ሞተ ማለት ነው። ይህ ካልኾነማ! ይላል ቄርሎስ የሞተውና መከራ የተቀበለው ማን ነው? ረሲኣን እንደሚሉት የሞተውና መከራ የተቀበለው ዕሩቅ ብእሲ ነው ከተባለ፣ ዕሩቅ ብእሲ ዓለምን አዳነው ማለት ነዋ! ብሎ በዲያድርስና በደቀመዛሙርቱ ይዘብትባቸዋል።

በወንጌል የተመዘገቡ የክርስቶስ ሥራዎች፣ አይሁድ «ግብር ሠናይ» ብለው የሰየሙት፣ «ተአምራቱ፤ «ዕርፈት» ብለው የሰየሙት የእግዚአብሔር ልጅነቱ፣ አምላካዊውም ኾነ ሰብአዊውም ኾነ ምድራዊ ያው ያንዱ የሥግው ቃል ነው። ከሥጋዌ በኋላ ይህ የቃል ነው፤ ያኛው የሥጋ ነው አይባልምና። ያለ ምንም ጥርጥር ኃይሉም ድካሙም በተዋሕዶ ሰው የኾነው አምላክ ያደረገው ነው። በክርስቶስ ሥጋዌ ምንታዌ የለምና፤ «ነሥአ ዘኢዚአሁ» ቃል የራሱ ያልነበረውን ሥጋን ተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ኾነ እንጂ፤ «አካላዊ ተዋሕዶ» ለሚሉትም ሲመልስ «አርአያ ገብር ሥጋና መለኮታዊ ቃል ባሕርያቸውን ትተው ተዋሐዱ አይባሉም። አካል ያለ ባሕርይ፤ ባሕርይ ያለ አካል አይኖርም፤ አይታወቅም። አካል የሌለው ባሕርይ፣ ባሕርይ የሌለው አካል የለም። ስለዚህ ሥግው ቃል አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው» ብሎአል።

በአንቀጸ ተዋሕዶ «ኮነ» ውሳጤን ያመለክታል ለሚሉት ሲመልስ፣ «ቃል ሥጋ ኮነ» (ቃል ሥጋ ኾነ) ሲባል፣ ቃል ተለውጦ ሥጋ ኾነ ማለት አይደለም፤ ሥጋም ወደ አምላክነት ተለወጠ ማለት አይደለም፤ በማይመረመር የተዋሕዶ ምሥጢር «እንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ፣ ወእንቲአሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል በተዋሕዶተ መለኮት» በተዋሕዶ የቃል ሀብት ለሥጋ፣ የሥጋ ሀብት ለቃል ኾነ እንጂ። ምሥጢረ ተዋሕዶን በይበልጥ ለማስረዳት፤ ቄርሎስ ብዙ ምሳሌዎችንና መረጃዎችን ያቀርባል። ከነዚህም አንዱ የኢሳይያስ ፍህም ነው፤ እንጨቱ (ከሰሉ) ከእሳት ተዋሕዶ የእሳቱን ሀብት የራሱ አድርጓል፤ ነገር ግን እሳቱ ወደ እንጨትነት አልተለወጠም፤ እንጨቱም መጠኑን፣ ቅርጹን አልለቀቀም፤ መለኮት ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ቢወሰንም፣ ምሉእነቱን አልቀቀቀም ሥጋም በተዋሕዶተ መለኮት የባሕርይ አምላክ ቢኾን ውስንነቱን አልቀቀቀም። ሌላው የቄርሎስ የታወቀ ምሳሌ የብረትና የእሳት ተዋሕዶ ነው፤ ብረት ከእሳት ሲገባ፣ ከእሳት ሲዋሐድ መጠኑን፣ ቅርጹን፣ ወርዱን፣ ቁመቱን ሳይለቅ የእሳቱን ሀብት ወርሶ፣ ሙሉ ኹለንታው ፍጹም እሳት እንደሚኾን፣ እሳቱም የእሳትነት ባሕርዩን፣ ጠባዩን ሳይተው በብረቱ መጠን የብረቱን ቅርጽ እንደሚይዝ፣ ኋላም አንጥረኛ በመዶሻ ሲያለዝበው፣ በመጋዝ ሲተረትረው፣ በብረትና በእሳት መካከል ምንም ልዩነት እንደማይታይ ውሳጤ፣ ቱስሕት፣ ቡዓዴ፣ ሕድረትም የሌለበት የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶም እንደዚሁ ነው። በኃይልም በድካምም ቡዓዴ፣ ውላጤ የሉምና መናፍቃን ከቅዱሳት አገኘን እያሉ ለስሕተታቸው ድጋፍ የሚሰጡ እየመሰሏቸው፣ የሚጠቅሷቸውንና ለሐሳባቸው እንዲስማማላቸው አጣመው የሚተረጒሟቸውን ሲነቅፍ ቄርሎስ እንዲህ ይላል፤ «ዘርእየ ኪያየ ርእዮ ለአቡየ፤ አነ ወአብ አሐዱ ንሕነ» ያለው እሱ «አብ የአብየኒ» ብሎ የተናገረው ነው። «ትፈቅዱ ትቅትሉኒ ብእሴ ዘጽድቀ እነግረክሙ» ያለው እሱ «ወለተ ኢያኤሮስን፣ ወልደ መበለትን፣ አልዓዛርን በቃሉ አዝዞ በቅዱሳት እጆቹ ይዞ ዳሶ ያስነሣው ነው። ስለዚህ ከተዋሕዶ በኋላ፣ ኹለቱ ባሕርያት በምንታዌ «በኹለትነት» አሉ ብሎ ማመን ወይም ለሌላው ማስተማር፤ አማኑኤልን ኹለት መልክ አለው ማለት ነው።

የሥግው ቃልን አንድ ባሕርይ የሚያስተምር ቄርሎስ፣ እንደ አቡሊናርዮ (አፖሊናርዮስ) የሥጋን ህልውና ከነባቢት፣ ከለባዊት፣ ከሕያዊት ነፍስ ለይቶ በነፍስ ቦታ መለኮትን ተክቶ፣ ቃልን ለሥጋ ምልአተ አካል አድርጎ አይደለም፤ ወይም በኋላ እንደ ተነሣው እንደ አውጣኪ፣ የሥጋን ከዊን አጥፍቶ ለውጦ ሥጋን የመለኮት ተገገር አድርጎ፣ መለኮት ሥጋን ዋጠው መጠጠው ብሎ አይደለም። እንደ መምሕሮቹ እንደነ አትናቴዎስ ቃል ከድንግል የነሣው ሥጋ ለባዊት፣ ነባቢት፣ ሕያዊት ነፍስ ያለው መኾንን በትክክል ያስተምራል። እንደነአቡሊናርዮስ አስተሳሰብ ለባዊው አሳቢው የሰው ክፍል ከተዋሕዶ ውጭ ከኾነማ?! ኃጢአትን አስቦና አጥንቶ የሠራው የሰው አካል አልዳነም ማለት ነዋ?! ይላል ቄርሎስ። የእንዚናዙ ሊቅ ጳጳስ ጎርጎርዮስ እንዳለውም፣ ያልነሣውን አዳነው ሊባል አይቻልም። ለብሶ ለዘአበሰ መባሉም ፍጹሙን የሰው አካል ነው።

ሥጋን እንጂ ነፍስን አልነሣም የሚሉ የአቡሊናርዮ ደቀመዛሙርት፣ መሳልሰው የሚጠቅሱትን (ዮሐ 1÷14) ቄርሎስ ሲተረጒም፣ ወንጌላዊው ዮሐንስ «ቃል ሥጋ ኾነ» ማለቱ፣ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ወልድ ዋሕድ ሰው ኾነ ማለቱ ነው ብሏል። (ኢዮኤል 2÷28) እሌኑ መንፈስየ ላዕለ ኵሉ ዘሥጋ ያለውን በመጥቀስ፣ ሥጋ የሚለው ቃል ቆዳውን ብቻ እንደማያመለክትና ፍጹም ሰውነትን የሚያመለክት መኾኑን በማብራራት ይኸው ሊቅ ያስተምራል። «ሥጋ» ማለት እነሱ እንደሚሉት ነፍስ የሌለው ቆዳ?! ከኾነማ ነቢዩ በትንቢቱ የተናገረው «የእግዚአብሔር መንፈስ፣ ነፍስ ለሌለው ቆዳ ተሰጠ ማለታቸው ነዋ! ይላል ሊቁ ቄርሎስ። የአቡሊናርዮስ ፍሬዎች ምናልባት ልብ ገዝተው ከስሕተታቸው ቢመለሱ በማለት፣ ትምህርቱንም ከቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሰ ያስተላለፍላቸዋል (ዕብራ 2÷14፣ ዮሐ 12÷27-28። ማቴ 26÷37-38። ሉቃ 23÷46)። ኹለት ባሕርይ የሚሉ ኹሉ፣ ያን ጊዜም ኾነ አሁን የሚጠቅሱት፣ በወንጌል የተጻፉትን የክርስቶስን መከራ መስቀልና የድካሙን ድርጊቶች ባንድ ወገን፤ ኃይሉንና ተአምራቱን በሌላ ወገን አድርገው ነው፤ ነገር ግን ቄርሎስ ባለመሰልቸት በየቦታው ይመልስላቸዋል።

ከሰባቱ አጽራኀ መስቀል አንዱ፣ «አምላኪየ አምላኪየ ለምንት ተኀድገኒ» ነው። ይህን እነሱ የድካም የብቸኝነት ምልክት አድርገው ይመድቡታል፤ እሱ ግን እንዲህ ይላል፤ ክርስቶስ ይህን ጩኸት ያሰማው፣ ርዳታ ፈልጎ ብቸኝነት አጥቅቶት አይደለም፤ ወይም እነሱ እንደሚሉት ያደረበት ቃል ተለይቶት አይደለም። የክርስቶስ ሞት ለቤዛ ስለኾነ፣ ድምፁ የተሰማው ኃጢአትን ከማያውቅ፣ በበደሉ፤ በኃጢአቱ ከፈጣሪው ተለይቶ ለኖረ፣ ለሰው ቤዛ መከራ የተቀበለ የሥግው ቃል ድምፅ ነው። ሰይጣን ድል፣

ተነሥቶ እኛም የአዲስ ሕይወት ባለቤት እንኾን ዘንድ፣ የክርስቶስ መከራ መቀበል አስፈላጊ ነበርና:: አዳምን ለማዳን የእግዚአብሔር ልጅ ዳግማይ አዳም ኹኖ ለመከራ ቀረበ:: ሰይጣንም ኃጢአትን የማያውቅ ኹኖ ቢያገኘው ደነገጠ፤ ድል ኾነ:: ዮሐንስ አፈወርቅም ከቄርሎስ ቀደም ብሎ የሞትን መሸነፍና የትንሣኤን ድል በጻፈበት አንቀጹ እንደ ተናገረው «የሚበላ መስሎት ጎረሰው፤ መራራ ቢኾንበት ተፋው» ብሏል:: ይህም ማለት ሰይጣን ሥግው ቃልን ዕሩቅ ብእሲ መስሎት ተጠጋው፤ ፈተነው፤ ሥግው ቃል መኾኑን ሲረዳ ትቶት ሸሸ ማለት ነው:: ተልባ መስሎሽ ሰናፍጭ ትቀምሽ እንዲሉ::

ሊቃውንት በየድርሳናቸው የተመዘገበው ትምህርታቸው ሁሉ የሚያመለክተው፣ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን ነው:: መናፍቃንን በገቡለት ገብቶ ምክንያት ማሳጣት ተገቢ ስለሆነ፣ ቄርሎስም መናፍቃን በየጊዜው የወሰዱትን ንባብ ይከታተል ነበር:: በቄርሎስ 2÷8-9 «ኵሉ መለኮቱ ኀደረ በሥጋ ሰብእ» ፍጹም መለኮቱ በሰው ሥጋ አደረ» ያለውን ይዘው ቃል በሥጋ አደረ ለሚሉት ሲመልስ፣ በአንቀጸ ሥጋዌ ኀድረት ቦታ የለውም:: ከድንግል ማርያም የተወለደውን ዕሩቅ ብእሲ ብለው መለኮታዊ ቃል አደረበት ከአሉማ?! ክርስቶስን ጸዋሬ እግዚአብሔር ማድረጋቸው ነው:: «ኀደረ» በቅዱሳን እንደሚደረገው ምሥጢራዊ ብቃት አይደለም:: እንደ ነፍስና እንደ ሥጋ ተዋሕዶ ማለት ነው:: በሌላ አንጻር ግን በኀደረ በተሠገወና በኮነ መካከል ልዩነት አለ:: ቃል ሰው ሆነ ማለት እግዚአብሔር በሰው አደረ ከማለት ጋር እንደማይመሳሰል::

ቄርሎስ በእስክንድርያ ይህንን ሲያስተምር፣ በዘመኑ የቍስጥንጥንያ ኤጲስቆጶስ የነበረው ንስጥሮስ ደግሞ፣ ከመምህሩ ከዲያድርስ ያገኘውን የሁለት ባሕርይና የኀድረት ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማስገባት ይጣጣር ነበር:: ይህ የንስጥሮስ የኀድረት ትምህርት በእስክንድርያ እንደ ተሰማ፣ ቅዱስ ቄርሎስ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት የትንሣኤን በዓል መልእክት ሲያስተላልፍ፣ (በ429 ዓ.ም ኹል ጊዜ የበዐላትን መዋያ ቀኖች የሚያውጀው የእስክንደርያ ሊቀ ጳጳስ እንዲሆን የሠለስቱ ምእት ቀኖና ያዛል::) ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ናት፤ የሚል ንባብ ያለበት መልእክት ጨምሮ አስተላለፈ:: ከዚህም በማያያዝ በናትሩን በረኻ የሚኖሩትን መነኮሳትና ባሕታውያን ሰብስቦ በቍስጥንጥንያ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ አይደለችም የሚባል ክህደት ተነሥቷልና በነገሩ እንዲያዝኑበት ገለጠላቸው:: እስከዚህ ድረስ ቅዱስ ቄርሎስ የንስጥሮስን ስም ጠርቶ አልተናገረም:: ነገሩን የገለጠው ራሱ ንስጥሮስ ነው:: ቅዱስ ቄርሎስ ባስተላለፈው መልእክት ማርያም «ወላዲተ አምላክ» የሚል ንባብ ስላገኘ ማርያም ወላዲተ አምላክ አይደለችም የሚል መልስ ወደ ቄርሎስ ላከ:: በዚህ ጊዜ ቄርሎስ በሁኔታው አዝኖ፣ በቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያት አበው ያቋስተማሩትን አዲስ ነገር መፍጠር፣ የቤተ ክርስቲያንን ጤናማ ትምህርት የሚያደናቅፍና ቤተ ክርስቲያንን የሚጎዳት መሆኑን በመግለጥ፣ ከስሕተቱ እንዲመለስ ጻፈለት:: ይህ የመጀመሪያው የቅዱስ ቄርሎስ መልእክት ነው::

ንስጥሮስ የቄርሎስን ምክርና ትምህርት ሳይቀበል፣ እንዲያውም ነገሩን የሚያባብስ፣ በመጀመሪያ የገለጥነውን የኀድረትና የሁለት ባሕርይ ትምህርቱን እና ከመጽሐፍ ቅዱስ የወሰዳቸውንም ጥቅሶች ጽፎ ለቄርሎስ ላከለት:: ንስጥሮስ በአውዶክስያና በቴዎዶስዮስ ዘንድ ባለሟል ስለነበር፣ ቄርሎስ ይፈራኛል የሚል ግምት ሳይኖረው አልቀረም:: ቄርሎስ ግን ምንም እንኳ ይህንን ቢረዳው፣ ነገሩን በብልኀት አለዝቦ ነበር የያዘው:: ስለዚህም በ430 ዓ.ም ሁለተኛውን መልእክቱን አዘጋጅቶ ይልክለታል:: ይኸኛው የቄርሎስ መልእክት የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ከሐዋርያት ተቀብለው ይዘዉት የኖሩትን የምስጢረ ሥጋዌ ትምህርት ነበር:: በዚህ ጊዜ ንስጥሮስ ረዳት ለማግኘት ወደ ሮማው ፓፓ ወደ ሠለስቲኖስ መጻጻፍ ጀመረ:: የሮማው ፓፓ ግን መልእክቱን አልተቀበለውም:: ምክንያቱም የሮም ቤተ ክርስቲያን ያወገዘቻቸውን የፔላግያኖስን ተከታዮች ንስጥሮስ ተቀብሎ አማካሪው አድርጎ አስቀምጧቸው ስለ ነበር ነው::

ቄርሎስም ምክሩና ማባበሉ ውጤት እንዳላስገኘ ስላየ፣ ለሦስተኛ ጊዜ 12 አንቀጽ ያለውን በተዋሕዶ ትምህርት ላይ ውላጤን ቱስሕትን፣ ምትሐትን፣ ሕድረትን፣ ቡዓዴን የሚያስተማሩ መናፍቃንን የሚያወግዝ መልእክት ላከ:: ይህ መልእክት ለንስጥሮስ ከመድረሱ ከ11 ቀን በፊት፣ ንጉሡም የነገሩን መባባስ ፈርቶ ጉባኤ ተሠርቶ በጉባኤ እንዲታይ አዋጅ ነግሮ ነበር:: ጉባኤው እንዲደረግ የተወሰነው በኤፌሶን (ታናሽ እስያ) በ431 ዓ.ም ሰኔ ሰባት ቀን የጰራቅሊጦስ ዕለት ነበር:: ነገር ግን ከሩቅ አገሮች የሚመጡት ኤጲስ ቆጶሳት ስለዘገዩ ሰሰኔ 22 ቀን ተላለፈ:: በዚህ ጉባኤ ተካፋይ ለመሆን የብዙ አገሮች ሊቃነ ጳጳሳት ተሰብስበው ነበር:: ንስጥሮስም ከሁሉ አስቀድሞ 16 ግብረ አበሮቹን ኤጲስ ቆጶሳት ይዞ በብዙ የቍስጥንጥንያ ቤተ መንግሥት ወታደሮች ታጅቦ ኤፌሶን ገባ:: ቄርሎስም ከእስክንድርያ ሊቀ ዲያቆኑን ኋላም ወራሹን ዲዮስቆሮስንና ሌሎች 50 ኤጲስ ቆጶሳትን አስከትሎ ኤፌሶን ደረሰ:: የኤፌሶን ሊቀ ጳጳሳት ሜምኖን አስተናጋጅ እንደመሆኑ መጠን በጉባኤው የሚቀመጡትን ተወካዮችና በማስተናበር የሚረዱትን ለመምረጥ አርባ ከሚሆኑ የሀገረ ስብከቱ ኤጲስ ቆጶሳት ጋር ስብሰባ አድርጎ ሰንብቶ ነበር:: በመካከል የኢየሩሳሌሙ ኢዮቤናልዮስና የተሰሎንቄው ፍላብያኖስ ጉባኤው ሲጀመር ሲል ደረሱ:: ከሁሉ ተለይቶ የቀረ፣ በቅርብ በጎረቤት ሀገረ ስብከት ያለው፣ የአንጾኪያው ዮሐንስ ብቻ ነበር:: ዮሐንስ ዘአንጾኪያ ያልመጣው የንስጥሮስ የተማሪ ቤት ጓደኛና «ለኀድረት ትምህርትም ተቆርቋሪና ደጋፊ ስለነበረ ነው» ንስጥሮስን ለመደገፍ አድማ ሲያደርግ ሰንብቶ ነበር የሚሉም አሉ:: ይኸውም ሲታወቅ ጉባኤው እሱን በመጠባበቅ ላይ ሳለ፣ «እኔ ብዘገይም ጉባኤውን ጀምሩት» ብሎ ለቄርሎስ መልእክት ልኮለታል፤ ለምን እንደሚዘገይ ግን መልእክቱ አይገልጥም:: አንዳንድ ባለ ታሪኮች ደግሞ ምንም እንኳ ዮሐንስ ዘአንጾኪያ የንስጥሮስን አሳብ ደጋፊ መሆኑ ባያጠራጥርም፣ የዚያን ጊዜው መዘግየቱ በጉዞ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ይላሉ:: እነዚህ ሰዎች እንደሚሉት ለወዳጁና ለሃይማኖት ወንድሙ ለንስጥሮስ በጉባኤው ቀርቦ ቢከራከርለት እንጂ መቅረቱ ስለማይጠቅመው፣ በጉዞ ምክንያት ዘገየ ማለቱ የሚያሳምን አስተያየት ሲመስል፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ የቦታ ርቀትና የጉዞ መሆኑን ለማመን የሚያስቸግር ግልጥ ያልሆነ አስቸጋሪ ምክንያት አለ፤ ይኸውም ከሱው ጋር እንደሱም ጥሪው የደረሳቸው የሩቆች ከኢየሩሌም ከመካከለኛው ምሥራቅና ከግብጽ ሲመጡ ለኤፌሶን ድንበርተኛ የሆነችው፣ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ የዘገየው መንገዱ ስለራቀበት ይሆናል የሚለው ግምት እውነት አይመስልም:: የዮሐንስ መቅረት ንስጥሮስን የሚደግፍ አድማ ሲጐነጕን ለመሆኑ፣ ምልክትና ፍንጭ የሚሰጡ አያሌ ምክንያቶች አሉ:: ከነዚህም አንዱ የሚከተለው ነው:: በጉባኤው መጀመሪያ ቀን፣ ንስጥሮስ ወደ ጉባኤው ቀርቦ ሐሳቡን ገልጦ እንዲናገር ሲጠየቅ፣ ጉባኤው በሙሉ ካልተሰበሰበ አልቀርብም አለ:: በጉባኤው ያልነበረው ዮሐንስ ብቻ ነበር እንጂ፣ ሌሎቹ በሙሉ ነበሩ:: ነገር ግን ንስጥሮስ፣ «ጉባኤው በሙሉ ካልተሰበሰቡ ያለው፣ ዮሐንስ የማይመጣ መሆኑን ለንስጥሮስ በቅድሚያ ቢያሳውቀው ነው::

ዮሐንስ ዘአንጾኪያ በመዘግየቱና ንስጥሮስም ቀርቦ እንዲያስረዳ ከጉባኤው ለቀረበለት ጥያቄ እሺ ብሎ ባለመቅረቡ፣ ጉባኤውን ለማሰናከል በዮሐንስና በንስጥሮስ የተታታ አድማ መኖሩን፣ ቅዱስ ቄርሎስ ተረዳው:: የጉባኤው ሊቀ መንበር እንደ መሆኑ፣ ባለው ኃላፊነት ለተሰበሰቡት የቤተ ክርስቲያን አባቶች የሚከተለውን መግለጫ ሰጣቸው:: ንስጥሮስም ሆነ ዮሐንስ በየፈለጉት ቢያመካኙም፣ «እኛ የመጣንበትን ሥራ ሠርተን ወደ የሀገረ ስብከታችን መመለስ አለብን ብሎ፣ ለተሰበሰቡት 200 ኤጲስ ቆጶሳት ገለጠላቸው:: እነሱም ባንድ ድምጽ ተስማምተው በቄርሎስ ሊቀ መንበርነት፣ ሰኔ 22 ቀን በእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጉባኤው ተጀመረ:: በጉባኤው መጀመሪያ ላይ የጉባኤ ኒቅያ አንቀጸ ሃይማኖት ተነበበ:: ከዚያ በኋላ ቅዱስ ቄርሎስ ወደ ንስጥሮስ የላከው ሁለተኛው መልእክት ተነበበ:: ምንባቡ ሲያበቃ ምሥጢሩ ከኒቅያው ጉባኤ ጋር ተመሳክሮ ከኒቅያ አባቶች ትምህርት ጋር አንድ ሁኖ ስለ ተገኘ፣ ጉባኤው በሙሉ ድምፅ ተስማምቶ ተቀብሎታል::

ጉባኤው በሁለተኛው ስብሰባ ያዳመጠው ንስጥሮስ ለቄርሎስ የመለሰውን ጽሑፍ ነው፤ ይህንም የጉባኤው አባላት መረመሩት፤ ብዙም ተወያዩበት፤ ነገር ግን «ኀደረ» የሚለው የንስጥሮስ እምነት «ተሰብአ ወተሠገወ ኮነ ብእሴ» ከሚለው ጋር ስላልተስማማ ጉባኤው አልተቀበለውም:: በሦስተኛው ስብሰባ በውግዘት ማስጠንቀቂያ የታጠሩ አሥራ ሁለት አንቀጾችን የያዘ ሦስተኛው የቄርሎስ መልእክት ተነበበ:: በዚህ ጊዜ የጉባኤው አባሎች ጳጳሳት ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ ቴዎፍሎስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ድረስ (412) የነበሩ ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንት ያስተማሩባቸውን መጻሕፍት ከቄርሎስ ትምህርት ጋር ማወዳደርና ማመሳከር ጀመሩ:: ከታዩትም የሊቃውንት መጻሕፍት የቅዱስ አትናቴዎስ ከእስክንድርያ፣ የአምብሮሲዮስ ከምዕራብ፣ የጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ፤ የባስልዮስ ዘቂሣርያና የጎርጎርዮስ ዘኑሲስ (ቀጶዶቅያ የምስራቅ ክፍል) መጻሕፍት ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: የቄርሎስ ትምህርት ከኒቂያ ሊቃውንት ትምህርት ጋር የንባብም ሆነ የምሥጢር ልዩነት እንደሌለው በሙሉ ድምፅ በጉባኤው ተመስክሯል::

በመጨረሻም ለንስጥሮስ ፍርድ እንዳይጎድልበት በማለት፣ መልእክቶቹን ሰብስበው ከነዚህ ከላይ ከጠቀስናቸው መጻሕፍት ጋር አመሳክረውለታል፤ ነገር ግን አሁንም የንስጥሮስ ክሕደት የሚጠጋበት ስላላገኙ፣ ንስጥሮስ ተሳስቷል፤ ከስሕተቱ አልመለሰም ካለ፣ ትምህርቱም እሱም ከሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የተለዩ ናቸው፤ ሲሉ አስታወቁ፤ ቄርሎስ የጉኤው ሊቀ መንበር ስለሆነ፣ የጉባኤውን አስተያየትና ከስሕተቱ ቢመለስ ግን ነገሩ እንደሚበርድ ለንስጥሮስ ሳይገልጥለት እንዳልቀረ ግምት አለ:: ነገር ግን ንስጥሮስ የእልህና የትዕቢት ወኔ አድሮበት አልመለስም በማለቱ፣ ጉባኤው ያስተላለፈው ውግዘት ተፈጽሞበታል:: በቅዱስ ቄርሎስ የተመራውና ሁለት መቶ አባላት ያሉበት ይህ የኤፌሶን ጉባኤ ሦስተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሲኖዶስ ነው:: እነዚህም «ኀደረት» የሚለውን ከላይ የድያድርስን ከታች የንስጥሮስን ትምህርት አውግዘው «ተዋሕዶ» በሚለው ትምህርት ተስማምተው ተመልሰዋል:: ድንግል ማርያምም፣ ቅድመ ዓለም የነበረውን አምላክ በዘመን፣ በሥጋ ስለ ወለደችው በአማን ወላዲተ አምላክ ናት ብለው የሐዋርያትን ትምህርት በውሳኔያቸው አጽድቀዋል::

ቴዎድሮስና ቴዎዶሪጦስ ግን፣ በመጀመሪያ እንደ ተናገርነው የንስጥሮስ ግብረ አበሮች ስለ ነበሩ የጉባኤውን ውሳኔ አልደገፍንም ለማለት ድምፅ ሳይሰጡ ቀርተዋል::

ከአራት ቀን በኋላ ሰኔ 26 ቀን ዮሐንስ ዘአንጾኪያ ከአድማ ጓደኞቹ ጋር አብሮ ሲመክር ሰንብቶ ወደ ኤፌሶን መጣ:: በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የታወቀ ሀገረ ስብከት የሌላቸወና በቤተ ክርስቲንም በነበሩበት ጊዜ ሥርዓት ሳይጠብቁ በመገኘታቸው ከመረነት ሥልጣን ተወግደው የሚኖሩ 43 የሚያህሉ አርሶ ፈረሶች አብረውት ነበሩ:: ዮሐንስ ኤፌሶን እንደ ደረሰ ጉባኤው የተስማማበትን ትምህርተ ሃይማኖትና የንስጥሮስን መወገዝ በሰማ ጊዜ በጣም ተናዶ አብረዉት ከመጡት ጋር ስብሰባ አደረገ:: በዚህ ጊዜ ቴዎድሮስና ቴዎዶሪጦስም ለንስጥሮስ ያላቸውን ድጋፍ ለመግለጥ ሲሉ ከሱው ጋር አንድ ሁነው በጉባኤው ተገኙ:: ይህ በጠርሴስ ቁልቅያ የተደረገው የዮሐንስ ዘአንጾኪያ ጉባኤ በኤፌሶን የተወሰነውን ለመከለስ ብዙ ታግሎ ነበር፤ ነገር ግን ዮሐንስም ሆነ ግብረ አበሮቹ ንስጥሮስን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመመለስ አልቻሉም፡ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በፊት በአትናቴዎስ አሁን በቄርሎስ ምክንያት ለተዋሕዶ ሃይማኖት ምስክር ሆነች::

ቄርሎስ ወደ እስክንድርያ ከተመለሰ በኋላ ዮሐንስ ዘአንጾኪያና አብረዉት የነበሩት የንስጥሮስ ደጋፊዎች ቄርሎስን ለማውገዝ መክረው ነበር፤ ነገር ግን ውግዘቱ በተንኮል እንጂ በእውነት ስላልነበረ ቄርሎስን የሚያስር አልነበረም:: ንስጥሮስም ከቤተ ክርስቲያን ተለይቶ በተወገዘ በአራት ዓመቱ 435 ዓ.ም ወደ ግብጽ ሔዶ በአክሚም ይኖር ነበር፤ ከዚያም 16 ዓመት ቆይቶ በ451 ዓ.ም ሞተ::

የተዋሕዶ ሃይማኖትን መመሪያዎች ካጠናከረና ንስጥሮስንም ካወገዘ በኋላ የኤፌሶን ጉባኤ ስምንት ቀኖናዎችን ሠርቷል:: እነዚህም በሰባተኛው ቀኖና በኒቅያ ጉባኤ ላይ ምንም ዓይነት ንባብ እንዳይቀነስ ወይም እንዳይጨመር ወስኗል:: በስምንተኛው ቀኖና የቆጵሮስ ቤተ ክርስቲያን ከአንጾኪያ ተለይታ ራሷን በራሷ እንድታስተዳድር ተፈቅዶላታል:: (አብያተ ክርስቲያናት እንዳይከፋፈሉ ክርስትናን ከተቀበሉበት መንበር ሥር መሆን አለባቸው፤ የሚለውን የሠለስቱ ምእት ቀኖና ለመሻር ሳይሆን አንጾኪያ ከቆጵሮስ ጋር በባሕር እንጂ በየብስ መገናኛ ስላልነበራት የቆጵሮስ ምእመናንና ካህናትም በሀገራቸው መንበር ለማቋቋም በብዛትም በዓይነትም ብቁዎች ስለሆኑ ነው::) በተጨማሪም ይህ ጉባኤ የፔላግያኖስን ትምህርት በድጋሚ አውግዟል:: ፔላጊዮስ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ እንግሊዛዊ የአየር ላንድ መነኩሴ ነው:: ትምህርቱም የአርዮስና የግኖስቲኮች ቅልቅል ነው:: የፐላጊዮስ ሐሳቦች የሚከተሉት ናቸው:: ሀ/ ክርስቶስ የሚሰገድለት አምላክ ስለሆነ አይደለም:: ለ/ አዳም ባይበድልም መሞት ነበረበት:: ሐ/ የአዳም በደል የጎዳው ራሱን ብቻ ነው ወደ ዘሮቹ አልተላለፈም ስለዚህም ሕፃናት በሚወለዱበት ጊዜ አዳም ከመውደቁ በፊት እንደ ነበረው ንጽሐ ጠባይዕ ሳያድፍባቸው ይወለዳል:: መ/ የሰው ዘር በራሱ ሥራ እንጂ በአዳም በደል አልሞተም አይሞትምም:: በክርስቶስ መነሣትም አይነሣም:: ሠ/ ኦሪትም እንደ ወንጌል ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊመራ ይችላል:: ረ/ ክርስቶስም ሳይመጣ ሰው ያለ ኃጢአት ሊኖር ይችል ነበር ይላል:: ከሀሳቦቹ ዋናዎቹ እነዚህ ናቸው፤ ይህ ትምህርት ቀደም ሲል በሮም ተወግዞ ነበር፤ አኹንም በኤፌሶን ጉባኤ እንደገና ተወግዟል::

በንስጥሮስ ደጋፊዎችና በተዋሕዶዎች መካከል ጠብና ጥላቻ እየተባባሰ ስለሔደ የቊስጥንጥንያ ቤተ መንግሥት በነገሩ አስቦበት ያን ጊዜ በትሩፋቱና በተባሕትዎው የታወቀው ስምዖን ዘዓምድ ባስታራቂነት እንዲገባ ከቤተ መንግሥት መልእክት ደረሰው፤

ስምያን ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ሲል ለማስታረቅ ሞክሮ ነገሩን ጥቂት አብርዶት ነበር: ነገር ግን የንስጥሮስ ክሕደት ውስጥ ውስጡን እየተሳበ ምድረ ሶርያን ሲያጥለቀልቃት ኾነ:: የቴዎድሮስ ደቀመዝሙር ኢባስ (ኢባን) የሚባለው ነብጽቢን አጠገብ በኡር (ኤዴሳ ሮሐ) የነበረውን የኦርቶዶክሳውን ትምህርት ቤት ለንስጥሮሳውያን ማሠልጠኛ አደረገው:: ይህም ኹኖ አንድ አካል፤ አንድ ባሕርይ በማለት የኤፌሶንን ጉባኤ ውሳኔና የቄርሎስን ትምህርት ያከበሩ ሶርያውያን ጳጳሳትና ምእመናን እምነታቸውን ተከላክለው ጠብቀው ለማቆየት ከንስጥሮሳውያን ጋር ትግላቸውን አላቋረጡም ነበር::

ኋላም ዘይኑን (ዚኖን) የተባለው የቊስጥንጥንያ ንጉሥ (474-491) ጠቡን ለማብረድ ይረዳ እንደኾነ ብሎ በ489 ዓ.ም በኡር የነበረውን ትምህርት ቤት ዘጋው:: ንስጥሮሳውያንም ምሽጋቸው ይህ ትምህርት ቤት ስለነበር ሶርያን እየለቀቁ ወደ ፐርሺያ (ፋርስ ኢራን) ሔዱ:: በዚያም በርቡማ በሚባለው አለቃቸው አማካይነት ትምህርታቸውን ማስፋፋት ጀመሩ፤ እስከ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ማለት እስላም ፋርስን እስከያዘበት ጊዜ ድረስ ሲስፋፉ ቆይተው እስልምና ሲመጣ ብዙዎቹ ወደ እስልምና ገቡ:: ጥቂቶቹም በመካከለኛው ምሥራቅ በታናሽ እስያ ድንበር ላይ እስካሁን ይገኛሉ:: ካህናት፣ ኤጲስ ቆጶሳትና ፓትርያርክ እያሉ ይሾማሉ:: የንስጥሮሳውያን ስብከት ቻይና ደርሶ እንደነበር ይነገራል::